# በኑሩንበርግ ከተማ (ጀርመን) የተካሄደውን ህዝባዊ ስብሰባ አስመልክቶ የተዘጋጀ ዘገባ

ፌብሩዋሪ 17-18 ቀን 2012 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ህዝብ የፃነት ተስፋው፣ ሃላፊነት በጎደላቸው መሪዎች በየዘመናቱ መዳረሻ ሲነጠቅ ኖሯል። የህዝቡና የሀገሪቱ ህልውና በፖለቲካ ውጥንቅጥ ውስጥ ከገባ እነሆ በርካታ ዓስርተ-ዓመታት ተቆጥረዋል። በሀገራችን ብሄራዊ የመብት ረገጣና ጭቆናን ለማስቀረት፣ ሁሉም ዜጎች፣ በእኩልነት፣ በመቻቻል፣ በነፃነትና በመከባበር የሚኖሩባት የተስፋ ምድር እንድትሆን ለማድረግ ቀደም ሲል የተጀመረው ህዝባዊ እምቢተኝነትና የመብት ማስከበር ትግል ዛሬም ቢሆን ከ40 ዓመታት መራራ የትግል ጉዞ በኋላ ገና እልባት አላገኘም።

ይህ ቀደም ሲል በአብዮት መባቻ፣ በፀና አለት ላይ፣ በህያው የተጋድሎ መድብል የተወጠነው፣ በጭቆና አልገዛም ባይነት ህዝባዊ አመፅ ቀዳማይ ምእራፍ ታሪካዊ የተጋድሎ ጉዞ ከጊዜ ወደ ጊዜ የበለጠ እየተወሳሰበና እልህ አስጨራሽ እየሆነ መጥቷል። በቅርብ ዓመታት የታየው የ1997ቱ ህዝባዊ የለውጥ ተነሳሽነትና ግፊትም ቢሆን ትግሉን አቀናጅቶ በአግባቡ ሊመራው የሚችል መሪ ድርጅት ባለማግኘቱ ሳቢያ የአምባገነኖች ሰለባ ሆኖ ቀርቷል። በአሁኑ ወቅት በሀገራችን፣ በሁሉም መስክ ሚዛን ደፍቶ ትግሉን ወደላቀ ምእራፍ ለማሸጋገር አለመቻሉ በራሱ፣ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ምን ያህል አጣብቂኝ ውስጥ እንደገባ በጉልህ የሚያመለክት ነው።

የትግሉ ባህርይ ውስብስብ በመሆኑ ሳቢያ፣ የተከፈለው መስዋእትነትና ያስቆጠረው እድሜ ተዳምረው የለውጥ አራማጆችን የተስፋ ጉዞ እልህ አስጨራሽ ብቻ ሳይሆን አጠያያቂ እያደረገው መጥቷል። ስለሆነም፣ የማለዳውን የተስፋ ምናባችንን መዳረሻ ለማወቅ በጨለማ የትግል ንቃቃት እንድናሙልቅም አስገድዶናል። ኦሮሞ ሲተርት **"ካን ዳባታኒ ዳካኒ፣ ታአኒ ቡኬሳኒ"** ይላል። "ቆመው የፈጩትን፣ ተቀምጠው ያቦኩታል" እንደ ማለት ነው። በእኛ ሀገር የፖለቲካ ቅኝት ቆመን የፈጨነውን ቆመን ለማቡካት እንኳ ከህወሃት በስተቀር ሌላ በለስ የቀናው ያለ አይመስለንም።

ከዚህ ጭብጥ በመነሳት፣ **የወቅቱ የሀገራችን የፖለቲካ ምህዳር መጥበብ ያሳሰበው የኢትዮጵያ የፖለቲካና ሲቪክ ማህበራት አንድነት ድርጅት በጀርመን እነሆ ፌብሩዋሪ 18 ቀን 2012 ዓ.ም እ.አ.አ በኑሩንምበርግ ከተማ ታላቅ ህዝባዊ የምክክር መድረክ አዘጋጅቶ ነበር። በዚህ መድረክ ላይ ጥሪ**





**የተደረገላቸው የክብር እንግዶች የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሲቪክ ማህበራት፣ የሃይማኖት መሪዎችን ጨምሮ በጠቅላላው ከ300 በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ተገኝተዋል።**

በፕሮግራሙ መሠረት ቀደም ብሎ፣ ዓርብ ፌብሩዋሪ 17 ቀን 2012 ዓ.ም እ.አ.አ ከሂዩማን ራይት ዎች (Human Right Watch) ጋር በትብብር በተዘጋጀው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ በርካታ የህግ ጠበቆች፣ የፖለቲካ ድርጅት ተጠሪዎች፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች፣ የበጎ አድራጎት ድርጅት ተወካዮች፣ ጥሪ ተደረገላቸው እንግዶችና የኢትዮጵያውያን ስደተኞች ተወካዮች በስፍራው ተገኝተዋል።

በሂዩማን ራይት ዎች (Human Right Watch) እና ከተለያዩ ድርጅቶች ተወክለው በመጡ እንግዶች የስደተኛውን ችግር አስመልክቶ ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡ ሲሆን፣ አያይዘውም፣ ይህን ከጊዜ ወደ ጊዜ አሳሳቢ እየሆነ የመጣውን የስደተኛውን አብይ ችግር ለመፍታት በሚቻልበት ሁኔታ አስመልክቶ በርካታ አስተያየቶች ሰንዝረዋል። በቀረቡት ሀሳቦች ላይ ጥያቄና መልስ የተካሄደ ሲሆን፣ በተለይ የወቅቱ የኢትዮጵያን ስደተኛ ጉዳይ በተመለከተ በእለቱ የተገኙት የክብር እንግዳ አቶ ኦባንግ ሜቶ (ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ) መስራችና መሪ በስፍራው ለተገኙት እንግዶች ሰፊ ማብራሪያ በመስጠት በስፍራው ለተገኙ እንግዶችና ጋዜጠኞች የኢትዮጵያውያን ሰብዓዊ መብት መረገጥና ወቅታዊውን

የስደተኞችን ችግር በማስመልከት ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ንግግር አድርገዋል። በንግግራቸው ላይ ካነሱዋቸው መሠረታዊ ነጥቦች መካከል፦



- የኢትዮጵያ ስደተኞች ጉዳይ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ሀገራት ትኩረት እንዳልተሰጠውና ይህም አግባብ እንዳልሆነ፣ በኢትዮጵያ ያለው የሰብዓዊ መብት ጥሰት በአፈፃፀሙ ባህሪ ካልሆነ በስተቀር በሌሎች ሀገራት ከሚታየው አሰቃቂ ሁኔታ የሚሻልበት አንዳችነገር የለውም በማለት ካስረዱ በኋላ፣
- የስደተኛው ወቅታዊ ችግር ለመፍታት መጣር ብቻ ሳይሆን፣ በሀገር ውስጥ የሚካሄደውን የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ረገጣ ማስቆም እጅግ አስፈላጊና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ አብይ ተግባር በመሆኑ፣ በዚህ ረገድ፣ እስካሁን እንደታየው፣ በምዕራባውያን ዘንድ ተገቢው ትኩረት እየተሰጠው አይደለም በማለት አሳሰበው፣



- ስደተኞች ከሀገራቸው ለመውጣት የሚገደዱት በሥርዓቱ አስከፊነትና በሚደርስባቸው የመብት ረገጣና የጭቆና ጫና ሳቢያ ነው። የውጭ መንግስታት የወያኔን ሥርዓት ከመደገፍ ተቆጥበው የህዝቡን መሠረታዊ የመብት ረገጣና የህግ ጥሰት ችግር ለመፍታት የሚያስችል አወንታዊ እርምጃ ሊወሰዱ እንደሚገባ አፅንኦ በመስጠት አስረድተዋል። በማጠቃለያቸውም፣
- የኢትዮጵያ ችግር የሀብት ሳይሆን የአመራር ችግር በመሆኑ፣ አመራሩን በማስተካከል ረገድ በሁሉም ዘርፍ ጥረት ማድረግ ቀዳሚው ተግባር ሊሆን እንደሚገባ ካመለከቱ በኋላ፣
- የስደተኛውን ችግር ለዘለቄታ መፍታት የሚቻለው በሀገር ውስጥ ያለውን አስከፊ ሁኔታ ሲሻሻልና የሥርዓት ለውጥ ማድረግ ሲቻል ብቻ እንደሆነ አፅንዖት ሰጥተው ለተሰብሳቢው አስገንዝበዋል።

በስፍራው ከተገኙ እንግዶች መካከል፦

- የሂዩማን ራይት ዎች ተወካዮች፣
- የረድኤት ድርጅት ተወካዮች፣
- የኢትዮጵያ ስደተኞችን ጉዳይ የሚከታተሉ የህግ ጠበቆች፣
- ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች፣
- የጋዜጣ፣ የቴሌቪዥን፣ የሬዲዮ ወኪሎች እና
- ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ተወካዮች ይገኙበታል።

ቅዳሜ በፌብርዋሪ 18 ቀን 2012 ዓ.ም፣ የተደረገው ህዝባዊ የምክክር መድረክ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት፦ ፕሮግራሙ በ13፡00 ሰዓት ተጀምሮ በ19፡00 ሰዓት ድረስ የ6፡00 ሰዓት ቆይታ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ስብሰባው ከታቀደለት ዓላማ አኳያ ስኬታማ ነበር ማለት ይቻላል። በተለይ በስብሰባው ላይ የሃይማኖት አባቶችን ጨምሮ ሌሎች የፖለቲካና የስቪክ ማህበራትን ተወካዮች የተገኙ ሲሆን፣ በተለይ የአቶ ኦባንግ ሜቶ በክብር እንግድነት በስፍራው መገኘት የሁሉንም ቀልብ የሳበና የስብሰባውን መንፈስ በአወንታ አስመዝግቦ ያለፈ ልዩ ግምትና ድምቀት የተቸረው ነበር።

በስብሰባው የተገኙት እንግዶች፦

1. **አቶ ኦባንግ ሜቶ፣ የእለቱ የክብር እንግዳ፣ (ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ መስራችና የድርጅቱ መሪ)**
2. **የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ - በጀርመን - ባየር አካባቢ 2 ተወካዮች፣**
3. **የኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ አባላት - በጀርመን - ባየር አካባቢ ተወካይ፣**
4. **የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ - ተወካይ፣**
5. **የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ተወካይ፣**
6. **የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ - ዲሞክራሲ ተወካይ፣**
7. **የእንደዜጋ መስራችና አስተባባሪ፣**

8. የኢሳት ሬድዮና ቴሌቪዥን እና
9. ሌሎች ቁጥራቸው ከ300 በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ተገኝተዋል።

ስብሰባውን በመክፈቻ ንግግር የከፈቱት የአዘጋጅ ኮሚቴው አስተባባሪ አቶ በላይ ወንዳፍራሽ እንደተናገሩት፣ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን እጅግ አሳሳቢ የሆነውን የዜጎችን መብት ረገጣ ለማስቆም በሚደረው ወሳኝ ፍልሚያ፣ የወጣቱ ተሳትፎ የበለጠ ለማሳደግና ተጨማሪ የትግል አጋር ሃይል ሆኖ ከአንድነት ሃይሎች ጎራ በቀዳሚነት እንዲሰለፍ ማስቻል ነው ካሉ በኋላ፣ የወጣቱን የትግል መንፈስ የሚያነሳሳና በትግሉ አውድ ዙሪያ ወጥ ሀገራዊ ራእይ የሚያስጨብጥ የጋራ የመግባቢያና መረዳጃ ስልት ነድፎ መንቀሳቀስ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ አስገንዝበዋል። አያይዘውም፣ በአሁኑ ወቅት በአዲስ የትግል መንፈስ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ማዕከል ያደረገ፣ የዓላማና የትግል አንድነትን የሚያስተሳስርና የሚገነባ ጠንካራ መሠረት ያለው ሁለገብ ማእቀፍ ውስጥ መሰባሰብ አስፈላጊ መሆኑን በማመልከት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ አሳሳቢ እየሆነ የመጣውን የስደተኛውን ችግር ለመፍታት የሚያስችል የተሻለ አደረጃጀት እስከአሁን ስላልነበር ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ለአያሌ ችግሮች ተጋልጠው ቆይተዋል። ይህንኑን ችግር በጋራ ለመቅረፍ የሚያስችልና ሀገርን ከጥፋት ለማዳን በሚደረገው ርብርብ ጉልህ አስተዋፅኦ ለማድረግ ይቻለን ዘንድ በጋራ መግባባትና መሥራት እጅግ አስፈላጊያችን በመሆኑ ሳቢያ፣ እነሆ የኢትዮጵያ የፖለቲካና ሲቪክ ማህበራት አንድነት ድርጅትን ለማቋቋም ችለናል ብለዋል።

በማያያዝም፣ በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምን፣ የግዛትና የህዝብ ሉዓላዊነቷን የሚያከብር፣ ማንኛውም ሀገራዊ አጀንዳ አለኝ የሚል የፖለቲካም ሆነ የሲቪክ ስብስብ፣ እንዲሁም ግለሰብ ጭምር ተባብሮ




ለመስራት ድርጅታቸው ዝግጁ መሆኑን በመግለፅ፣ ለኢትዮጵያ ትንሳኤ ከዘረኝነትና ከጎጠኝነት የፀዳ፣ በእኩልነትና በመከባበር ላይ የተመሰረተ የበሰለ የፖለቲካም ሆነ የልማትና የእድገት ሥራዎችን ከሚያራምዱ ሃይሎች ጋር ለአንዲት ኢትዮጵያ ትንሳኤ እጅ ለእጅ ተያይዘን በመቻቻል በጋራ መግባባት እንሥራ በማለት ጥሪ አድርገዋል።

በማስከተልም፣ የድርጅቱ ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ፀሀፊ፣ የድርጅቱን አላማና አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም፣ የስብሰባውን ጥሪ አስፈላጊነት በማስመልከት አጭር ንግግር ያደረጉ ሲሆን። በንግግራቸው ላይ እንዳመለከቱት በአሁኑ ወቅት የስደተኛው ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከተ በመምጣቱ ሳቢያ ችግሩ በዛው ልክ እየተባባሰ ሄዷል ካሉ በኋላ፣ በተለይ በአንዳንድ ሀገራት በኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ እየተፈፀመ ያለው አሳዛኝ ሁኔታ ወደሌላም እንዳይዛመት በሁሉም ደረጃ አስፈላጊው ጥረትም ሊደረግ እንደሚገባ አበክረው አስረድተዋል። አያይዘውም እንደዚህ አይነቱን መሠረታዊና አሳሳቢ ጉዳይ ለመፍታት የሚያስችል አቅም ከወዲሁ ለመፍጠር እንዲቻል በማሰብ ይህ ዝግጅት እንደተደረገና ሁሉን አቀፍ በሆነው ድርጅታዊ ማእቀፍ ስር ተሰባስቦ በየጊዜው እየተገናኙ የጋራን ችግር በጋራ ለመፍታት የሚያስችል ስትራቴጂ ነድፎ መሥራትና ለስደተኛው መብት መከበር በጥምረት መስራት አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው ሲሉ አስምረውበታል።

በማያያዝም፣ የድርጅታቸውን መመስረት አስፈላጊነቱንና አላማ ሲያብራሩ፣ በተለይም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን በሚመለከት ማንኛውም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አጀንዳ እና የዜጎችን መብት ለማስከበስከበር በሚደረግ ገምቢ እንቅስቃሴ አወንታዊ ምላሽ መስጠት የሚያስችል አቅም ስደተኛው ይኖረው ዘንድ ለማስቻል ታቅዶ የተቋቋመ ድርጅት እንደሆነና በዚህ አጋጣሚ፣ ወጣቱ ትውልድ የኢትዮጵያን የወደፊት እጣ ፈንታ በመወሰን ረገድ ያለውን አብይ ድርሻ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የነቃና የላቀ ተሳትፎ በፖለቲካው፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊው ዘርፍ እንዲኖረው ለማስቻል የታቀደ ነው በማለት አስረድተው፣ የዛሬውም የውይይት መድረክ የተዘጋጀው ከዚህ ፅኑ ዓላማ በመነሳት በቀጣይ በስደተኛውም ሆነ በሀገር ጉዳይ ላይ አመርቂ ሥራ ለመስራት በማቀድ እንደሆነ ጠቅለል አድርገው አስረድተዋል።

በመጨረሻም፣ ድርጅታቸው **የኢትዮጵያ ፖለቲካና ሲቪክ ማህበራት አንድነት ድርጅት - በጀርመን የሚል ህጋዊ ስያሜ ያለው አካል ነው ካሉ በኋላ፣ በአሁኑ ወቅት፣ በስፋት በስደት ዓለም ያለውን ዜጋ ሁሉ በሀገሩ ጉዳይ ላይ ጉልህ ሚና እንዲኖረውና የትግል ተመክሮና ልምድ እንዲያገኝ በማድረግ ረገድ የጎላ ድርሻ** ይኖረዋል በማለት ንግግራቸውን ቋጭተዋል።

ከዚያ በማስከተል **"ምን ያደርጋል ሀገር"** በሚል እርእስ ግጥም ተነቦ የእለቱ የክብር እንግዳ አቶ ኦባንግ ሜቶ መድረኩን እንዲይዙ ተደረገ።



አቶ ኦባንግ በንግግራቸው መግቢያ ላይ፣ **"እኔ የመጣሁት ከእናንተ ለመስማት ነው፣ ዘወትር በአካል አብሬአችሁ ባልገኝም በመንፈስ ግን ከእናንተ ጋር ነኝ ካሉ በኋላ፣ እኔ የማደርገው የፖለቲካ ንግግር አይደለም፣ ሆኖም ግን ስለራሳችን እኛው ኢትዮጵያውያን እየተገኛኘን ካልተወያየን ሌላ ማን ሊደርስልን ይችላል?"** በማለት ተሰብሳቢውን ጠይቀዋል፡፡

**"ሁላችንም ሀገራችንን እንወዳለን ነገር ግን በሀሳብ አለመግባባት ሳቢያ እንገፋፋለን። ምንም እንኳ የደረጀ ሀብት ባይኖረን በጉልበት ግን ሀብታሞች ነን። ህዝብን የሚወድ መንግስት ስለሌ ነው እንጅ፣ ኢትዮጵያ የበረከት ሀገር ነች"** በማለት ገልፀው በ2005 ዓ.ም በጋምቤላ ከ420 ሰዎች በላይ በመጨፍጨፋቸው ሳቢያ የኢትዮጵያውያንን ሰብዓዊ መብት ለማስከበር ትግል እንደጀመሩ በማስረዳት አያይዘው፣ ስለ ዜጎች መብት ትግል ሲናገሩ፣ **"ሁሉም ነፃ ካልወጣ ማንም ነፃ ሊወጣ አይችልም፣ ስንፈጠር ማንኛችንም ብንሆን የጎሳ ካባ ለብሰን አልተወለድንም። እንደማንኛውም ዜጋ ሰው ሆነን ብቻ ነው የተፈጠርነው"** በማለት፣ የአበባ ተክልን ምሳሌ አድርገው፣ **"አንድ አይነት አበባ በአትክልት ስፍራ ብቻውን ቢለማ ምንም ያህል ቀልብ ሊስብ አይችልም፣ ተፈላጊነቱም ያንኑ ያህል ነው። ነገር ግን የተለያዩ ቀለም ያላቸው አበቦች በአንድ ላይ ቢለሙ ግን ምንኛ የተዋቡ ይሆናሉ ዋጋቸውም በዚያው ልክ ውድ ይሆናል"** በማለት የሁሉም ኢትዮጵያውያን ጎሳዎችና ብሄሮች አብሮነት፣ እኩልነት፣ ሰላምና ፍቅር መከባበርና መቻቻል ለዛሬዋ ኢትዮጵያ ከምንጊዜውም በላይ ጠቀሜታው እጅግ የላቀ እንደሆነ አበክረው አስረድተዋል።



አቶ ኦባንግ ንግግራቸውን በመቀጠል፣ የኢትዮጵያ ችግር **"አንድ ሰው ይጋግራል፣ 200 ሰው ይበላል"** አይነት እንደሆነ በምሳሌ አስንዝበዋል። አያይዘውም፣ **"ኢትዮጵያውያን ከምንግዜም በበለጠ ወደ ተለያዩ ሀገራት በብዛት እየተሰደዱ ነው። ህዝብ ከሌለ ሀገርም የለም። ሀገር በራሱ ያለህዝብ ትርጉም የለውም። ይህ የሰራተኛ ሃይል ፍልሰት እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ነው"** ብለዋል። አያይዘውም፣ በቀጣይ ምን ሊደረግ እንደሚገባ ሲያስረዱ፣ **"ዛሬ ኢትዮጵያውያንን ለመርዳት አጋር አለ ወይ?"** በማለት ጠይቀው፣ **"በጋራ ያስተሳሰሩንን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶቻችንን መሰረት አድርገን፣ በተደራጀና በተቀናጀ መልክ የተነጠቅነውን መብት ለማስመለስ በፅኑ መታገል አለብን"** ብለዋል። አስከትለውም፣ **"ትግሉ ከፍተኛና ረዥም እንደመሆኑ መጠን፣ እጅ ለእጅ ተያይዘን በጋራ ተቧድነን ለሀገራችን አዲስ ተስፋ እውን መሆን ተግተን በጋራ፣ በፍቅር፣ በመቻቻልና በመግባባት መስራት ይጠበቅብናል"** በማለት አፅንኦት በመስጠት በተደጋጋሚ ለተሰበሰበው ህዝብ አስገንዝበዋል።

በማያያዝም፣ በሚከተሉት አቢይ ነጥቦች ዙሪያ ሀሳባቸውን በዝርዝር በማስረዳት ንግግራቸውን ይዘት አጠቃለዋል።

- **ትግላችን ኢትዮጵያ ነፃ እስከምትወጣ ድረስ አለመታከት በመሥራትና በመታገል ሊሆን ይገባል፣**
- **ኢትዮጵያን ለማዳን በፍቅር ካልሆነ በፀብ የሚደረገው የትግል ጉዞ የከፋ አደጋ ሊያስከትል ይችላል፣**
- **የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ የሚወሰነው በእኛው በኢትዮጵያውያን እጅ ብቻ ነው፣**
- **የዛሬው መሰባሰባችን ከትላንቱ ይልቅ ለቀሪው ትግላችን እጅግ ጠቀሜታ አለው፣**
- **ወያኔ ማለት ትግሬ ማለት ብቻ አይደለም፣ የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የጋምቤላ ወ.ዘ.ተ ወያኔ አለ፣**
- **ወያኔን እናስወግዳለን ስንል፣ ጨቋኝ ሥርዓቱን እንጅ ከትግሬ ጋር እንጣላለን ማለታችን አይደለም፣**
- **መሪዎችን ማምለክ ማቆም አለብን፣ መሪ ሳይሆን ሰው በሰውነቱ፣ ዜጋም በዜጋነቱ በቅድሚያ ሊከበር ይገባዋል፣**
- የኢትዮጵያ አትጠፋም አምላኳ ይጠብቃታል፣ እኛም የትልቅ ሀገር ልጆች ነን። ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ ትንሳኤ ተግባብተን፣ ተፈቃቅረን፣ ተባብረንና ተቀናጅተን እንሥራ በማለት የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ቀልብ የሳበና የገዛ፣ ከሁሉም ወገን አወንታዊ ምላሽ የተቸረው ሀገራዊ አንድነትንና ብሄራዊ መግባባትን የሚገነባ መልእክት አስተላልፈዋል።




ከዚያም በማስከተል፣ የተለያዩ የፖለቲካና የስቪክ ማህበራት ተወካዮች የድርጅታቸውን አቋም በማስመልከት አጫጭር ገለፃ ያደረጉ ሲሆን፣ የድርጅቶቹ ተወካዮች ባደረጉት ገለፃ በትግሉ ዙሪያ ተደጋግፎ ለመስራት ያላቸውን ተስፋ የገለፁ ሲሆን፣ ልዩነቶቻቸውን በማጥበብ ወደላቀ ትብብር ለመድረስ በሚያደርጉት ጥረትም ሆነ ሀገር ውስጥ የሚደገረውን የመስዋእትነት ትግል በፅኑ በመደገፍ ረገድ የሁሉም በጎፍቃደኝነትና ርብርብ እንደሚያሻው አስገኝዝበው ለጋራ የትግልና የትብብር መድረክ መፈጠር የበኩላቸውን ጥሪ አድርገዋል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የቀረበው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ESAT) እና ሬዲዮ ተወካይ ባደረጉት ንግግር ኢትዮጵያውያን በሚያደርጉት የመብት ትግል የሚዲያ አስፈላጊነት አጠያያቂ እንዳልሆነ አስምረው፣ በአሁኑ ጊዜ ለህዝቡ በቂ መረጃ ለመስጠት ድርጅታቸው ተግቶ እየሠራ በመሆኑ፣ በተለያየ የዓለም አካባቢ የሚገኙ ኢዮትጵያውያን ወገኖች ስለ ሀገራቸው ወቅታዊ ሁኔታ በቂ መረጃ እንዲያገኙ ለማድረግ ተችሏል ብለዋል። በማስከተልም፣ ለወደፊቱ ይህንኑ ተግባር የበለጠ አጠናክሮ ለማስቀጠል ባላቸው እቅድ መሰረት፣ ተግተው እየሠሩ መሆናቸውንና ገልፀው፣ ይህንኑ ተልእኮ በበለጠ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል የሁሉም ኢትዮጵያውያን ድጋፍና ርብርብ እንደሚያሻ አስገንዝበዋል።



በማስከተል፣ የተናገረው የወጣት ስደተኞች ተወካይ ሲሆን፣ የኢትዮጵያን ታሪካዊ ጥንታዊነትና ታላቅነት አስታወሶ፣ እስከአሁን ድረስ ኢትዮጵያ ከባህላዊ ሥርዓት መላቀቅ ባለመቻሏ እየታየ ላላው ሰው ሰራሽ ችግር ዳርጓታል በማለት አስገንዝቦ፣ ምንጊዜም ቢሆን፣ ሀገራችን ያጣችው ነገር ቢኖር፣ ሐብት ሳይሆን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና ህዝባዊ መሠረት ያለው መንግስት ነው፣ በዚህ ረገድ ከደርግ ውድቀት ማግስት በሀገራችን ይሰፍናል ብለን በተስፋ ስንጠባበቅ የቆየነው የፍትህና የሰብዓዊ መብት መከበር ጉዳይ እንደጉም በኖ ጠፍቷል ብሏል፡፡ አያይዞም የወገኖቻችን ሰቆቃ ያበቃ ዘንድ፣ የሀገራችን ህዝባዊ የሥልጣን ልዕልናና መብት ባለቤትነት፣ ብሔራዊ አንድነትና እኩልነት፣ ሀገራዊ ሉዓላዊነት፣ የአስተሳሰብና የእምነት ነፃነት ይረጋገጥ ዘንድ ተደራጅተንና ተግተን መታገል ታሪካዊ አደራችን ብቻ ሳይሆን የዜግነት ግዴታችንም ጭምር ነው በማለት አሰረግጦ ተናጋሯል። በመቀጠልም የትግል ወኔያችንና የጽናት መንፈሳችን የሚነቃቃው፣ ከልባችን በምንሻቸው የሀገራችን የፍትህና የነፃነት፣ የመብት ግቦች ላይ ያለን እምነት ሲታደስ እንደመሆኑ መጠን። ለዚህ ክቡር አላማ እጅ ለእጅ ተያይዘን እንድንነሳና በጋራ ሀገራዊና ወገናዊ ሃላፊነትን እንድንወጣ የከበረ ጥሪ መሳተላለፍ እንወዳለን በማለት ንግግሩን አጠናቋል።

በቀጣይ ንግግር ያደረገችው **የሴቶች ተወካይ ስትሆን፣** በንግግሯ ላይ እንዳለችው፣ በኢትዮጵያ ከግማሽ በላይ የጠቅላላውን የሀገሪቱን ህዝቡ ቁጥር የሚሸፍኑት ሴቶች መሆናቸው ገልፃ፣ በሀገራችን የሴቶች ጥያቄና ችግር ገና አልተፈታም በማለት ገልፃ፣ **ሴቶች እንደማንኛውም የህብረተሰብ አባል፣ በአንድ ሀገር ላይ የሚከሰት፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ቸግሮች ተካፋይ ናቸው በማለት፣ በኢትዮጵያ ባለው አምባገነን ሥርዓት፣ ሳቢያ የሴቶችን ጭቆና ድርብ ድርብርብ አድርጎታል ካለች በኋላ፣ የፖለቲካው ትርምስ ገፈት ቀማሾች በአመዛኙ ሴቶች ናቸው።** መውለድ ወንጀል የሆነበት ሀገር ቢኖር ኢትዮጵያ ብቻ ነች ማለት ይቻላላ በማለት፣ የሥርዓቱ አስከፊ ገፅታ ጠቅለል ባለ መልኩ አስረድታለች።

በማስከተልም፣ ሴት ልጆች በኢትዮጵያ፣ ህይወታቸው በሰቆቃ፣ ኑሮዋ ለአደጋ የተጋለጠ ነው። ወደ አረብ ሀገር ግርድና እተሰደዱ ከፎቅ የሚወረወሩ፣ በቢላዎ የሚተለተሉ፣ በወህኒ የሚጣሉ፣ በየበረሃው በምንገድ ላይ የሚደፈሩ፣ የሚገደሉ፣ የሚታፈኑ፣ በስደት ጉዞ እንደወጡ የሚቀሩ በርካቶች ናቸው። ይህ ሁሉ ከሥርዓቱ አስከፊነት የመነጨ የህዝብ በደልና የመብት ጥሰት ያስከተለው የመከራ ገፈትና ነው ብላለች። በመጨረሻም፣ እኛ ሴቶች በትግሉ አውድ ጉልህ ድርሻ ለማበርከት እንችል ዘንድ፣ የሁላችሁንም እገዛ እንሻለን። ወያኔ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የጣለውን የጭቆና ቀንበር ለመስበር በሚደረገው ሀገራዊ ትግል በቆራጥነት ተግተን እንድንነሳ የከበረ ጥሪያችንን በዚህ አጋጣሚ ለሁሉም ዜጎች ማስተላለፍ እንወዳለን። በማለት ለቀጣይ ትግል ጥሪ በማድረግ ሀሳቧን ደምድማለች።





ከዚህ በመቀጠል ለ1፡00 ሰዓት ያህል ለምሳ እረፍት ተደርጎ፣ ከምሳ መልስ ስብሰባው የቀጠለ ሲሆን፣ ቀደም ሲል በአቶ ኦባንግ ሜቶ የቀረበውን ሀሳብ መነሻ በማድረግ፣ ከቤቱ የተለያዩ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ቀርበው በአቶ ኦባንግ በስፋት በማብራሪያና ምላሽ ተሰጥቷል። ከቀረቡት ጥያቄዎችና ከተሰጡት አስተያየቶች መሃል ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል፦ ሀገር ቤት ስለሚንቀሳቀሰው ጥምረት ስለተሰኘው የፖለቲካ ድርጅት፣ በጋምቤላ ስለሚታየው ወቅታዊ ሁኔታ፣ ስለ ኢሳት ቴሌቪዥንና ሬዲዮ አገልግሎት፣ አለመግባባታችን እስከመቼ? በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ረገጣ ዙሪያ ሂዩማን ራይት ዎች እና አምስቲ ኢንተርናሽናል ምን እየሰሩ ነው፣ በኖርዌ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ጉዳይ በተመለከተ የቀረቡ ነበሩ።

አቶ ኦባንግም ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ሁሉ ተገቢውን ምላሽ የሰጡ ሲሆን፣ በተለይ ወቅታዊና አሳሳቢ በሆነው የኖርዌይ መንግስስት ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ የወሰደው እርምጃ በይፋ በማውገዝ፣ ዓለም አቀፉን ሰብአዊ መብት ድንጋጌ የሚፃረር ተግባር በመሆኑ በትግላቸው እንደሚገፉበት የገለፁ ሲሆን፣ ሁኔታው ተግባራዊ ከሆነ በተለያዩ ሀገራት ባሉ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ስደተኞችም ተመሳሳይ እድል እንዳይገጥማቸው ስጋታቸውን ገልፀዋል። የመፍትሄ ሀሳብ ሲሰጡ፣ ለዚህ ሁሉ እየዳረገንን ያለው በሀገራችን ያለው ጨቋኝ ሥርዓት ነው። ከዚህ አስከፊ ሥርዓት መላቀቅ ቀዳሚው ተግባራችን ሊሆን ይገባል ብለዋል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ፣ ለሚሰሩት የኢትዮጵያውያንን ሰብዓዊና ዲሞክራሲአዊ መብት የማስከበር ትግል ለማጠናከር ይረዳቸው ዘንድ፣ የጀመሩት በድህረ-ገፅ ፊርማ የማሰባሰብ ተግባር ስኬታማ እንዲሆን ሁሉም ዜጋ ፊርማቸውን እንዲያስቀምጡ ጥሪ አድርገዋል። በተለይም ስደተኞች የመኖሪያና የሥራ ፈቃድ ካገኙ በኋላ ከትግሉ ጎራ ያፈገፍጋሉ። ይህም የስደተኛውን ችግር በአግባቡ ለመፍታት መሰናክል ከመሆኑም ባሻገር፣ በሀገር ቤት ያለውን የመብት ረገጣ ለማስቆም በሚደረገው እልህ እጨራሽ ትግል ላይ አሉታዊ ጫና ፈጥሯል በሚለው ከፖለቲካ ድርጅት ተወካዮች በተሰነዘረው አስተያየት ላይ የበኩላቸውን አስተያት ሲገልፁ፦

- ኢትዮጵያ በኢትዮጵያውያን መሪዎች እየተመራች አይደለም፣
- ስለ እናንተ መብትና ነፃነት ሌላ ከሌላ ሥፍራ መጥቶ እንዲሞትላችሁ አትጠብቁ፣
- የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ  አሁን ባለው አዙሪት እንዲቀጥል ትፈልጋላችሁ ወይ?
- ትግላችሁ እስከ ወረቀት ድረስ ከሆነ እንኳን ሀገራችሁን፣ ራሳችሁንም ነፃ ማውጣት አትችሉም፣
- ለሰው ብላችሁ ሳይሆን ኢትዮጵያን ለማዳን ስትሉ አንድነታችሁንና ትግላችሁን ልታጠናክሩ ይገባል፣
- በኢትዮጵያ ጉዳይ ተስፋ መቁረጥ የለብንም፣ በፍቅር፣ በመግባባት፣ በመከባበር፣ በእኩልነት፣ በመደራጀትና አብሮ በመስራት ታላቅ ለውጥ ማምጣት እንችላለን።

በማለት ዜጎችን የትግል መንፈስን የሚያቀና፣ ወኔን የሚያድስ፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የሚገነባ፣ የስደተኛውን ሀገራዊ እይታ የሚያዳብር በብሄራዊ አጀንዳ ዙሪያ የመግባባት፣ የአንድነትና የመቻቻልን ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያስችል ንግግር ያደረጉ ሲሆን፣ ከተሰብሳቢው ይሰጥ ከነበረው አስተያየት ለመረዳት እንደተቻለው፣ ተስፋ የሚጣልበትና የሁሉንም ቀልብ የማረከ ነበር ማለት ይቻላል።

የአዘጋጅ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ በሰጠው አስተያየት እንደገለፀው፣ **ምንም እንኳ በአሁኑ ወቅት በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ ግለሰቦች ልብ በራሱ ጠረፍ መሽጎ ያለ ቢሆንም፣ የምንናፍቀውን የሰከነ ፖለቲካ ለማራመድና መቻቻልና መግባባትን ፈጥሮ በጋራ ለስደተኛው ደህንነትና ለዜጎች መብት መከበር ለመስራት ያስችለን ዘንድ ከሃሳብ ምንደኝነት ተላቀን ከአድማስ ባሻገር ለመነነው የነፃነት ምናባችን ቤዛ መሆን መቻል አለብን።** ስለሆነም በራሳችን የትግል ምህዋር ለመጓዝ ያስፈለገንን ይህንኑ ህልማችንን እውን ለማድረግ ባለን ቀና አስተሳሰብ ነው ብለዋል።

ቀጣዩ ፕሮግራም፣ የተካሄደው በኢትዮጵያ የመብት ትግል ህይወታቸውን ላጡ ሰማዕታት የህሊና ፀሎትና የሻማ ማብራት ሥነሥርዓት ነበር። **ሥነ-ሥርዓቱ በመንፈሳዊ አባቶች የተመራ ሲሆን፣ በወቅቱ በሰጡት አስተያየት የስብሰባው መንፈስ እጅግ ያስደሰታቸውና የኢትዮጵያዊነትን መንፈስ የሚያድስ፣** ለሀገራችን ትንሳኤ ተስፋ የሚያመለክት ጅማሮ እንደሆነና በቀጣይ የዜጎችንን መብት ለማስከበርና ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት በጋራ ለመስራት የሚያስችል ተመክሮ ሆኖ እንዳገኙት አስረድተዋል።




በመጨረሻም፣ ምንም እንኳ በአሁኑ ወቅት በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ ግለሰቦች ልብ በራሱ ጠረፍ መሽጎ ያለ ቢሆንም፣ የምንናፍቀውን የሰከነ ፖለቲካ ለማራመድና መቻቻልና መግባባትን ፈጥሮ በጋራ ለመስራት ያስችለን ዘንድ ከሃሳብ ምንደኝነት ተላቀን ከአድማስ ባሻገር ለመነነው የነፃነት ምናባችን ቤዛ መሆንና አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመመሥረት ይቻለን ዘንድ ለዕርቅ፣ ለፍትሕ፣ ለሰላምና ለአንድነት መቆም የሁሉም ኃላፊነት መሆኑን በመወሰን ስብሰባው ተደምድሟል፡፡

በመጨረሻም፣ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን በመርዳት ከፍተኛ እገዛ ለሚያደርጉ አንዷት ጀርመናዊት እና አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሽልማት ተሰጥቶ የእለቱ ስብሰባ ከ6፡00 ሰኣት ቆይታ በኋላ በ19፡00 ሰዓት በሰላም ተጠናቋል።

ኤፍሬም አበራ፡ eph.abera@yahoo.com እና
አክሊሉ ኃይሉ aklilu.h2@googlemail.com

## ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

# የኢትዮጵያውያን ፖለቲካና ሲቪክ ማኅበር አባላት አንድነት ድርጅት - በጀርመን

# Ethiopian Political & Civic Community Union – in Germany

……………………………………………………………………………………..

Date: 8/03/012

To: Mr. Obang Metho, Executive Director of the SMNE

**Acknowledgement**

We would like to officially forward our appreciation and many thanks to the SMNE and Mr. Obang Metho in particular in advance. We strongly support the SMNE principles of putting **"humanity before ethnicity,"** or any other distinctions that divide and dehumanize other human beings from ourselves; inspiring us to care about for others because **"none of us will be free until all are free."** Your effort in

advocating for human right and democracy is like a horizon of hope to Ethiopian people these days. We are very grateful to your organization and your work as a whole.

We have found that, it is an inspiring issue to act together for the betterment of Ethiopian people and New Ethiopia as whole. In this regard what the SMNE as an organization and particularly Mr. Obang personally doing so far has shown us a remarkable achievement.

Thus, we would like to follow your foot step and stand bold inline to the SMNE mission, mainly, in the area of combating injustice, inequality, and violation of human and democratic right inland and abroad of Ethiopia. Struggling to secure these core values of human dignity are among those front line objectives in our organization above all.

The Nuremburg – Germany, meeting on 18/02/012 was an inspiring meeting that alarmed every one of us to stand alert for a real and bright new Ethiopia. We realize that what you did so far with us in Nuremburg is a part of your noble mission. It witnesses how much your extensive effort and commitment is to support our shared vision.

In the end, we would like to confirm you once again that, we always work hard to make our shared vision real with regards to restoring peace, equality, democracy and human rights in Ethiopia in general.

Sincerely Yours,
EPCU – Nuremburg
Germany

**Schmittner Str.10 60489 Frankfurt am Main, Tel: – 0176-716793330, Fax:-**